የወ/መ/ቁጥር 159195

የልደታ ምድብ 1 ኛ ወንጀል ችሎት

ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፣ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ *መሳይ* **ተድላ ቀረበ**

ተከሳሽ፣ አቶ ሀብታሙ ሰቦቃ - ከማረሚያ ቤት ቀረበ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ቅጣት ለመወሰን ሲሆን በዚሁ *መሰረት*ም ፍ/ቤቱ ጉዳዩን *መ*ርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ *መ*ልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም *መ*ሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን *መ*ንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ *ሥ*ርዓት፤ *መ*ብትና ጥቅም *መ*ጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም *መ*ከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ 1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወሰነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ክብደት *መ*ዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን *መመ*ሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች *መ*ሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ተከሳሹ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ 1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 689/ በሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን *መመ*ሪያው አንቀፅ 13 *መ*ሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም *መ*ሰረት እንደሚወሰን *መመ*ሪያው በደነገገው *መ*ሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. *መ*ካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው በቤት በር ላይ በመሆኑና የደረሰው የንብረት ጉዳት መጠን ብዙ ባለመሆኑ የተፈፀመው ወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 689 ለወንጀሉ የተቀመጠው መነሻና መድረሻ ከአስር ቀን እስከ አንድ ሺህ ዘጠና አምስት ቀን ቀላል እስራት የቅጣት እርዝመት ለአራት ተከፍሎ ስሌቱን በመስራት የተገኘው ውጤት ደረጃ አንድ መቶ ቀን ቀላል እስራት ነው።

በዚህም መሰረት የተገኘው መነሻ ቅጣት በአባሪ አንድ እርከን 3 ላይ የሚታይ ሲሆን ፍቃደ ስልጣኑም/range/ ከሁለት ወር እስከ አምስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን በፍ/ቤቱ የተወሰነው መነሻ ቅጣት ሦስት ወር ከአስራ አምስት ቀን እስራት ነው።

ከዚህ በመነሳት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 84 እና 85 እንደተገለፀው የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስላላቀረበ ቅጣቱ ከዚህ ከመነሻ ቅጣቱ ከብዶ አልተወሰነም።

ተከሳሽም የቅጣት አስተያየት እንዲያቀርብ ተጠይቆ ድርጊቱን የፈፀምኩት በመጠጥ ኃይል ነው ቢልም በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ እንደ ቅጣት ማቅለያ ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም። በሌላ በኩል ግን ተከሳሽ ድርጊቱን መፈፀሙን በግልፅ ችሎት ያመነ ስለሆነ፤ ይህም መፀፀቱን ስለሚያመለክት፤ ይህ ደግሞ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82(1)(ሠ) ላይ እንደተመለከተው የቅጣት ማቅለያ ምክንያት ስለሆነ አሁን የቅጣት መነሻው ካረፈበት እርከን 3 በመመሪያው አንቀፅ 16(4) መሰረት ወደ እርከን 2 ዝቅ ይላል።

ስለሆነም በመነሻ እርከኑ የነበረው ቅጣት ከቀረበው ማቅለያ ምክንያት ጋር ተሰልቶ እርከን 2 ላይ ተወስኗል። በዚሁ እርከን የተቀመጠው ፈቃደ ስልጣን/Range/ ከአስር ቀን እስከ ሦስት ወር እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ፍ/ቤቱ የወንጀል ክብደቱንና የተከሳሹን የግል ሁኔታውን መዝኖ ተከሳሽ በአንድ ወር ቀላል እስራት እንዲቀጣ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት ተከሳሹ እጁ ከተያዘበት ጊዜ ጀምሮ በማሰብ
የተወሰነው የእስራት ቅጣት እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።